በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 201980

ቀን ፡- ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ መሠለ ማሚቶ - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ እሸቱ መኮንን - ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ።

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው። የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ። አመልካች በአጭር ሥነ-ሥርዓት ያቀረቡት ክስ ተጠሪ ላጋጠመው ችግር እንዲያውለው ለሠጠኋቸው ገንዘብ የቼክ ቁጥሩ 01960861 የሆነ ብር 120,000.00 የተጻፈበት ቼክ ፈርመው ሠጥተው ባንክ ለክፍያ ስሄድ ሂሳቡ በቂ ስንቅ የለውም ተብሎ የተመለሰ በመሆኑ ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል። ተጠሪ የመከላከያ ማስፈቀጃ ምክንያታቸው ተቀባይነት በማግኘቱ ያቀረቡት መልስ ለአመልካች የምመልሰው ገንዘብ የለም፣ ለአመልካችም የሰጠሁት ቼክ የለም። በክሱ የቀረበው ቼክ አመልካች ቤት ለሚጣለው ዕቁብ እኔ አባል በመሆኔ እጣ ወጥቶልኝ ብር

450,000.00 ገንዘብ ስወስድ ቀንና የገንዘብ መጠን የሌለው ቼክ ለእቁቡ ዳኛና ፀሀፊ በዋስትና የሰጠሁ ሲሆን አመልካች ራሱ ቼኩ ላይ ጽፎ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ላይ በቼኩ ምክንያት የወንጀል ክስ ቀርቦበት ቼኩን ለአመልካች አለመስጠቱንና ለዕቁብ ለዋስትና የተሰጠ ቼክ መሆኑ ተረጋግጦ ከክሱ በነጻ ተሰናብቷል፡፡ ቼኩ ለዕቁብ ዋስትና እንጂ ለአመልካች ያልተሰጠ መሆኑ ስለተረጋገጠ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራቀኙን አከራክሮ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ለቀረበው ክስ ቼኩና የባንክ ማረጋገጫ ቀርቧል፡፡ ለጉዳዩ የሰው ማስረጃ ሊሰማ አይገባም፡፡ የሰው ማስረጃ ከተሰማም የአመልካች ማስረጃም ሊሰማ ሲገባ በተጠሪ ምስክሮች ብቻ መወሰኑ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ቼክን መሠረት ያደረገው ክስ ውድቅ መደረጉ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 717 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አንጻር ለማየት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ አመልካች የሠው ማስረጃ ባለመዘርዘሩ አልተሰማለትም፡፡ ቼኩ ለዕቁብ ዋስትና የተሰጠ ነው፡፡ ለቼክ ክርክር የሠው ማስረጃ እንዳይቀርብ የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ ተረጋግጦ የተወሰነ ነው ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርከር፣ የሠበር አጣሪ ችሎት የያዘው ጭብጥን በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በአጭር ሥነ-ሥርዓት ያቀረቡት ክስ ተጠሪ ላጋጠመው ችግር እንዲያውለው ለሠጠኋቸው ገንዘብ የቼክ ቁጥሩ 01960861 የሆነ ብር 120,000.00 የተጻፈበት ቼክ ፈርመው ሠጥተው ባንክ ለክፍያ ስሄድ ሂሳቡ በቂ ስንቅ የለውም ተብሎ የተመለሰ በመሆኑ ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ የመከላከያ ማስፈቀጃ ምክንያታቸው ተቀባይነት በማግኘቱ ያቀረቡት መልስ ለአመልካች የምመልሰው ገንዘብ የለም፣ ለአመልካችም የሰጠሁት ቼክ የለም፡፡ በክሱ የቀረበው ቼክ አመልካች ቤት ለሚጣለው ዕቁብ እኔ አባል በመሆኔ እጣ ወጥቶልኝ ብር 450,000.00 ገንዘብ ስወስድ ቀንና የገንዘብ መጠን የሌለው ቼክ ለእቁቡ ዳኛና ፀሀፊ በዋስትና የሰጠሁ ሲሆን አመልካች ራሱ ቼኩ ላይ ጽፎ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሠረቱ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሀተታ የሌለበት ትዕዛዝ የያዘና ቼኩም እንደቀረበ የሚከፈል መሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር 827/ሀ/ እና 854 ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ቼኩ የታዘዘለት ሰው ቼኩን ይዞ እንደቀረበ ቼኩ ሊከፈል ይገባዋል፡፡ ቼክ አውጪውም ሆነ የጀርባ ፈራሚዎቹ ለቼኩ አከፋፈል በንግድ ሕግ ቁጥር 840 እና 868(ሐ) መሠረት ኃላፊዎች በመሆናቸው ቼክ ባልተከፈለ ጊዜ ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በአጭር ሥነ-ሥርዓት ክሱን ያቀረቡ ቢሆንም ተጠሪ ክሱን ለመከላከል

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ፍ/ቤቱ የተቀበለው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 291 አግባብ ክርክሩ በመደበኛው ሥርዓት የሚመራ ነው።

ተጠሪ ቼኩ ቀንና የገንዘብ መጠን የሌለው መሆኑን ገልጸው የተከራከሩ ሲሆን በቼክ ላይ የሚጻፉ አስፈላጊ መግለጫዎች ናቸዉ ተብለዉ በንግድ ሕግ አንቀጽ 827 ከፊደል ሀ እስከ ሠ ባሉት ንኡሳን አናቅጽ የተጠቀሱ መግለጫዎች(Contents)፡- ሀ) የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትእዛዝ፤ ለ) መክፈል የሚገባዉ ከፋይ ስም፤ ሐ) የሚከፈልበት ቦታ፤ መ) ቼኩ የወጣበት ቦታና ጊዜ እና ሠ) ቼኩን ያወጣዉ ሰዉ ፊርማ የሚሉ ናቸዉ።በዚሁ ሕግ አንቀጽ 828 ስር ባለዉ የመግቢያ ዐረፍተ ነገር ላይ እንደተመለከተዉ ከእነዚህ መግለጫዎች አንዱ እንኳን የሌለበት ሰነድ እንደ ቼክ እንደማይቆጠር ተመልክቷል።በዚህ ድንጋጌ ላይ "ከእነዚህ መግለጫዎች አንዱ እንኳን የሌለበት ሰነድ እንደ ቼክ አይቆጠርም" የሚለዉ አገላለጽ ላይ ላዩን ሲታይ ግልጽ ቢመስልም አገላለጹ የሚያገለግለዉ መግለጫዎቹ ያልተሟላ ቼክ በቼክ አዉጪዉ ተፈርሞ ለአምጪዉ በሚሰጥበት ጊዜ ነዉ ወይስ ቼኩ ለክፍያ ሲቀርብ ነዉ የሚለውን በመመልከት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 193270 ቼኩ በተሰጠ ጊዜ ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 አንጻር ቀንና የገንዘብ መጠኑ ባለመጻፉ የተሟላ ባለመሆኑ እንደ Blank Cheque የሚቆጠር ቢሆንም ቀንና የገንዘብ መጠን ተሞልቶ ለከፋዩ ባንክ በቀረበ ጊዜ ተሟልቶ ከቀረበ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 እና 828 ያስቀመጣቸዉን አንድን ሰነድ ቼክ የሚያሰኙ መገለጫዎችን የሚያሟላ ወይም እንደ ቼክ የሚቆጠር እና ሕጋዊ ዉጤት ያለው ነው በማለት አስገዳጅ ትርጉም የሠጠበት በመሆኑ እና አመልካች ለክፍያ ባንክ ያቀረቡት ቼክ በቂ ስንቅ የለውም መባሉ በቼኩ ላይ ያሉ መግለጫዎች ተሟልተው ለባንኩ መቅረቡን ስለሚያስገነዝብ ክስ የቀረበበት ቼኩ ሕጋዊ ውጤት ያለው ሠነድ ነው ብለናል።

ተጠሪ በሁለተኛ ደረጃ የሚከራከሩት እና የሥር ፍርድ ቤት የተቀበለው ቼኩ ለዕቁብ ዓላማ ለዋስትና የተሰጠ ነው የሚል ነው። ቼክ ተላላፊ የገንዘብ ሠነድ በመሆኑና በዋስትናነት አይሰጥም በሚል በሕግ የተደነገገ ክልከላ ባለመኖሩ በመርህ ደረጃ ቼክ ለዋስትና ሊሰጥ ይችላል። ሆኖም በሰበር መዝገብ ቁጥር 166392 ላይ በቀን 26/08/2012 ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ ላይ በመርህ ደረጃ አግባብነት ያለዉ የፍ/ብ/ህጉና የንግድ ህጉ ለቼክ የሰጡት ዋና ዓላማ ለመያዣነት እንዲያገለግል ነዉ ባይባልም እንደማንኛዉም ሊተላለፉ እንደሚችሉ ሰነዶች በመያዣነት ወይም በዋስትና ሊሰጥ እንደሚችልና ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን በንግድ ህጉና በፍ/ብ/ህጉ ላይ በተቀመጡት ግልፅ ድንጋጌዎች መመራት ይኖርበታል (የን/ህ/ቁ 950 ና ፍ/ብ/ህ/ቁ. 2866)። በተለይ የመያዣ ዉል ስምምነት በሚደረግ ጊዜ ዉሉ መከተል ስላለበት ፎርም በተመለከተም በግልፅ የተደነገገ ስለመሆኑ ከን/ህጉ ቁ. 952 እና የፍ/ብ/ህጉ ቁ. 2828 መመልከት ይቻላል። የመያዣ ወይም የዋስትና ዉል ህጉ በፅሑፍ በሰነድ ካልተደረጉ በህግ ፊት ዋጋ የላቸዉም (ፈራሽ ናቸዉ) በማለት ከደነገጋቸዉ ጥቂት የዉል ዓይነቶች ዉስጥ አንዱ ስለመሆኑ ግልፅ ነዉ (የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1725(ሀ)፤ 1922(1-3)፣ 2828(1-2))። ሌላዉ ደግሞ የመያዣዉ ስምምነት ለምን ግዴታ እንደተደረገ፣ የግዴታዉ መጠን (ከፍተኛ የገንዘብ ወሰን) በጥንቃቄ ግልፅ መደረግ እንዳለበትና ስምምነቱ የተደረገበት ቀን በግልፅ ልቀመጥ እንደሚገባ ህጉ የግድ ይላል (የፍ/ብ/ህ/አንቀጽ 2828 (1-2)፣ 2864-2866ና የን/ህ/ቁ. 952)። እነዚህ የህጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ካልተሟሉ የመያዣ ስምምነት ዉል አለ ማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ቼኩ የተሰጠዉ ለዋስትና ዓላማ እንደሆነ ተገልጾ በጽሁፍ የዋስትና ዉል ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር ቼክ ለዋስትና አላማ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት እንደሌለዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ቼኩን የሠጡት የዕቁብ ዕጣ ሲወጣላቸው ለዋስትና ዓላማ ከሆነ ይሕ ስለመሆኑ በጸሁፍ የተደረገ የመያዣ ውል (pledge) በማቅረብ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ቼክ ቁጥሩ ተገልጾ ለታወቀ ዕዳ መያዣ ስለመሆን አለመሆኑ በግራቀኙ ማስረጃ ሆነ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 መሰረት ተከራካሪዎች ካቀረቧቸው ማስረጃዎች በተጨማሪ ለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆነ የዕቁብ ዋስትና ውል ወይም መያዣ ውል ስለመኖር አለመኖሩ ጉዳዩን በማጣራት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከተውን አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ ኃላፊነቱን ሳይወጣ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 338113 ጥር 18 ቀን 2013 ዓ/ም እና የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32991 መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቼኩን የሠጡት ለዕቁብ ዕጣ ሲወጣላቸው ለዋስተና ወይም ለመያዣ መሆን አለመሆኑን በማስረጃ በማጣራት የመሠለውን እንዲወስን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩን መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም